## የማቴዎስ ፩ ሴቶች

# ማርያም

የጥናት መምሪያ

Selah
PAUSE • REFLECT



# መግቢያ

በማቴዎስ ፩ ውስጥ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የዘር ሐረግ ውስጥ የአምስት ሴቶችን ስም እናያለን። ለብዙዎቻችን የዘር ሐረግ መቁጠር ከመጽሐፍ ቅዱስ ንባባችን አብልጠን የምንወደው አካል ላይሆን ይችላል። አንዳንዶቻችን ከነጭራሹ ልንዘለው እንችላለን። ሆኖም፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተዘረዘሩት በእያንዳንዱ የዘር ሐረጎች ውስጥ ትኩረትን የሚስቡ አስደናቂ ነገሮችን እናያለን፣ ማቴዎስ ፩ም እንዲሁ ነው።

የሴቶች ወይም የእናቶች ስም በአይሁድ የዘር ሐረግ ውስጥ በተለምዶ አይጠቀሱም። በእውነቱ በአይሁድ ታሪክ ዝና የነበራቸውን ትውልዶች ብቻ በመጥቀስ፣ ሌሎችን በመዝለል የዘር ሐረጎችን በአጭሩ የሚጽፉ ሰዎች ስለነበሩ፣ በዘር ሐረግ ውስጥ መጠቀስ ራሱ በጣም ትልቅ ክብር ነበር። ይህንን ስናስብ እነዚህ አምስት ሴቶች ማለትም ትዕማር፣ ረዓብ፣ ሩት፣ ቤርሳቤህ እና የኢየሱስ እናት ማርያምን ማቴዎስ መጥቀሱ በእርግጥ ሊያስደንቀን ይጀምራል።

እነዚህ አምስት ሴቶች ሕይወታቸው ሲጠና ስለ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ስለ ወንጌል፣ እና ስለ እለት ተእለት ሕይወት የሚነግረን ነገር አለ።

© 2020 by Selah Ministries

Published by Selah Ministries
P.O. Box 479, Addis Ababa, Ethiopia

Published in Addis Ababa, Ethiopia
All rights reserved. No part of this publication may be reproduced in any form without permission from the publisher, except in the case of brief quotations embodied in other works or reviews.

All Scripture quotations are from the NASV Amharic Bible (Holy Bible, New Amharic Standard Version (Addisu Medebegna Tirgum)) Copyright © 2001 by Biblica, Inc.®
All rights reserved worldwide.

Illustrations
Front cover: Yikunoamlak Ayalew
Back cover: Ammanuel Anbessie

# ስለ ጥናት መምሪያው

የእግዚአብሔርን ቃል ለመረዳት ስንፈልግ መንፈስ ቅዱስ ዋና አስተማሪያችን መሆኑን መዘንጋት የለብንም። ኢየሱስ “መንፈስ ቅዱስ ሁሉን ነገር ያስተምራችኋል፤ እኔ የነገርኋችሁንም ሁሉ ያሳስባችኋል” ይለናል (ዮሐንስ 14፥26)። በጥናታችን ጊዜ መንፈስ ቅዱስ እንዲያስተምረን፣ እንዲለውጠን ከመጠየቅ ባሻገር የሚከተሉትን ይዘው መዘጋጀት ጠቃሚ ነው ብለን እናስባለን።

- መጽሐፍ ቅዱስ
- ማስታወሻ ደብተር (ሐሳብዎን ለማስፈሪያ ቦታ ስላለው ይህንን መምሪያ አትመው በማውጣት መጠቀም ይችላሉ)
- በመጽሐፍ ቅዱስዎ ወይም በማስታወሻዎ ውስጥ ለመጻፍ ቀለም ያላቸው እስኪብርቶዎች ወይም እርሳሶች

---

በዚህ ጥናት ውስጥ ሁሉ ራስዎን እነዚህን ጥያቄዎች እየጠየቁ ይሂዱ፥

- ይህ ክፍል ስለ እግዚአብሔር ልብ፣ መንገዶች፣ እና ባሕርይ ምን ይነግረኛል?
- ይህ ክፍል ወደ ኢየሱስ እና ወደ ወንጌል እንዴት ይጠቁማል?
- ልከተለው ወይም ላስወግደው የሚገባ ምሳሌ አለ? ከሆነስ፣ ምን ዓይነት ለውጥ ወይም ምላሽ መስጠት አለብኝ?

ተጓዳኙን የጥናት ቪዲዮ መመልከት ጠቃሚ ሆኖ ሊያገኙት ይችላሉ። ቪዲዮውን ከዚህ በታች ያለውን ምስል በመንካት ወይም በድህረ-ገፃችን
www.selahethiopia.org/mary ያገኙታል።



# ሉቃስ 1:26-56

በስድስተኛው ወር፣ እግዚአብሔር መልአኩ ገብርኤልን በገሊላ ወደምትገኘው ወደ ናዝሬት ከተማ ላከው፤ የተላከውም ከዳዊት ዘር ለሆነ ዮሴፍ ለሚባል ሰው ወደታጨች ወደ አንዲት ድንግል ነበር፤ የድንግሊቱም ስም ማርያም ነበረ። መልአኩም እርሷ ወዳለችበት ገብቶ፣ “እጅግ የተወደድሽ ሆይ፤ ሰላም ለአንቺ ይሁን፤ ጌታ ከአንቺ ጋር ነው፤ አንቺ የተባረክሽ ነሽ” አላት። ማርያምም በንግግሩ እጅግ በጣም ደን ግጣ፣ “ይህ ምን ዐይነት ሰላምታ ይሆን?” እያለች ነገሩን ታሰላስል ጀመር፤ መልአኩም እንዲህ አላት፤ “ማርያም ሆይ፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስ አግኝተሻልና አትፍሪ። እነሆ፤ ትፀንሻለሽ፤ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ፤ ስሙንም ኢየሱስ ትዪዋለሽ። እርሱም ታላቅ ይሆናል፤ የልዑል ልጅም ይባላል፤ ጌታ አምላክ የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል፤ በያዕቆብም ቤት ላይ ለዘላለም ይነግሣል፤ ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም።”

ማርያምም መልአኩን፣ “እኔ ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?” አለችው። መልአኩም መልሶ እንዲህ አላት፤ “መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፤ የልዑልም ኀይል ይጸልልሻል፤ ስለዚህ የሚወለደው ቅዱሱ ሕፃን፣ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል። እነሆ፤ ዘመድሽ ኤልሳቤጥም በስተ እርጅናዋ ወንድ ልጅ ፀንሳለች፤ መካን የተባለችውም ስድስተኛ ወሯን ይዛለች፤ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና።”

ማርያምም፣ “እነሆ፤ እኔ የጌታ ባሪያ ነኝ፤ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ” አለች። ከዚያም መልአኩ ተለይቶአት ሄደ። ማርያምም በዚያው ሰሞን በፍጥነት ተነሥታ ወደ ደጋው አገር፣ ወደ አንድ የይሁዳ ከተማ ሄደች፤ ወደ ዘካርያስ ቤትም ገብታ ለኤልሳቤጥ ሰላምታ አቀረበች።

ኤልሳቤጥም የማርያምን ሰላምታ በሰማች ጊዜ፣ ፅንሱ በማሕፀኗ ውስጥ ዘለለ፤ ኤልሳቤጥም በመንፈስ ቅዱስ ተሞላች፤ ድምፅዋን ከፍ አድርጋ እንዲህ አለች፤ “አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ፤ የማሕፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው። ስመሆኑ የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እኔ ማን ነኝ? እነሆ፤ የሰላምታሽ ድምፅ ጆሮዬ እንደ ገባ፣ በማሕፀኔ ያለው ፅንስ በደስታ ዘሎአልና። ጌታ ይፈጸማል ብሎ የነገራትን ያመነች እርሷ የተባረከች ናት!” ማርያምም እንዲህ አለች፤ “ነፍሴ ጌታን ከፍ ከፍ ታደርገዋለች፤ መንፈሴም በመድኀኒቴ በእግዚአብሔር ደስ ትሰኛለች፤ እርሱ የባሪያውን መዋረድ ተመልክቶአልና። ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል፤ ኀያል የሆነው እርሱ ታላቅ ነገር አድርጎልኛልና፤ ስሙም ቅዱስ ነው፤ ምሕረቱም ለሚፈሩት ከትውልድ እስከ ትውልድ ይኖራል። በክንዱ ብርቱ ሥራ ሠርቶአል፤ በልባቸው ሐሳብ የሚታበዩትን በትኖአቸዋል፤ ገዢዎችን ከዙፋናቸው አውርዶአቸዋል፤ ትሑታንን ግን ከፍ ከፍ አድርጎአቸዋል፤ የተራቡትን በበጎ ነገር አጥግቦአቸዋል፤ ሀብታሞችን ግን ባዶአቸውን ሰዶአቸዋል፤ ምሕረቱን በማስታወስ፣ ባሪያውን እስራኤልን ረድቶአል፤ ይህም ለአባቶቻችን እንደ ተናገረ፣ ለአብርሃምና ለዘሩ ያለውን ለዘላለም ለመጠበቅ ነው።” ማርያምም ሦስት ወር ያህል ኤልሳቤጥ ዘንድ ከቈየች በኋላ ወደ ቤቷ ተመለሰች።

# ማርያም

ሉቃስ 1:26-38 እናንብብ። በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ስለ ማርያም የተማርናቸውን ነገሮች ሁሉ እንዘርዝር።

በሉቃስ 1፥31-33፣ 35 ውስጥ መልአኩ ለማርያም ስለሚወለደው ልጅ ገልጧል። እነዚህን ጥቅሶች ስናነብ ስለ እርሱ (ስለሚወለደው ልጅ) ልናገኛቸው ከምንችላቸው ነገሮች ቢያንስ ስድስቱን እንጻፍ።

- ሉቃስ 1፥50-53ን እናንብብ። እግዚአብሔር ለእነዚህ የማህበረሰብ ክፍሎች ምን ያረጋል? በራሳችን አነጋገር/ቃላት እንጻፍ

እሱን የሚፈሩት ______________________________

ኩራተኞች ______________________________

ገዥዎች ______________________________

ትሑታን ______________________________

የተራቡት ______________________________

ሀብታሞች ______________________________

- በሉቃስ 1፥49-50 ውስጥ ማርያም በእግዚአብሄር ባህሪዎች ትደሰታለች። ማርያም የትኞቹን የእግዚአብሔር ባሕርያትን ትኩረት ትሰጣለች?

______________________________

______________________________

______________________________

- በእግዚአብሔር ባሕሪዎች ላይ ማሰላሰል በአምልኮአችን ላይ ምን አይነት ተጽዕኖ ያሳድራል?

- ሉቃስ 1፥51-53 በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ ማርያም የትኞቹን የእግዚአብሔር ሥራዎች ትጠቅሳለች?

- ዘፍጥረት 22፥16-18ን እናንብብ። የኢየሱስ ልደት እግዚአብሔር ለአብርሃም ከሰጠው ተስፋ ጋር እንዴት ተዛመደ? ማርያም ይህንን ሊመሰገን የሚገባው ነገር እንደሆነ እንዴት አሰበች?

- ምንም እንኳን አንድ ሰው ይህ ተአምር ይሆናል ብሎ ቢያምን እንኳን፣ የተአምሩ አካል መሆን ይፈልጋል ማለት አይደለም። ማርያም ስለተነገራት ትንቢት ተቃውሞ እንድታሰማ ወይም ምሬት እንዲሰማት ሊያረጋት የሚችሉ ነገሮች አሉ?

- መልአኩ በሉቃስ 1፥28 ማሪያምን የሚጠራበት መንገድ እጅግ ለየት ያለ አክብሮት የተላበሰ ነው። ይህ ለምን ይመስላችኋል? ለማሪያም እጅግ ትልቅ ክብር ሊኖረን የሚገባው ለምንድን ነው? ምክንያቶቹን አንድ በአንድ እንዘርዝር

- ኤልሳቤጥ ለማርያም ያቀረበችላት ሰላምታ ውስጥ እያንዳንዱ መግለጫ አስፈላጊነቱ ምንድነው (ቁ.42-45)? ማርያምስ ለዚህ ሰላምታ ምን ምላሽ ሰጠች?

- በሉቃስ 1፥48 ውስጥ ማርያም ለሀሴቷ ምን ምክንያትን ሰጠች?

- ማሪያም በታሪክ ውስጥ የክርስቶስ እናት የመሆን እንዲሁም ብቸኛዋ የፀነሰች ድንግል ሴት የመሆን ክብርና በረከት ያላት ፈሪሃ አምላክ ያላት አስደናቂ ሴት ነበረች። ይህ የማይሻር እውነት ቢሆንም፤ እሷን ከክርስቶስ አልቀን እንዳናስቀምጣት መጠንቀቅ አለብን። ከመጽሐፍ ቅዱስ ንባባችን፣ የማሪያም ሰው መሆንን በተመለከተ ምን እንማራለን?

- ማርያም እራሷን የጌታ “ባሪያ” ብላ ትጠራለች እናም ደግሞ እንደ ባሪያ እውነትም ስታገለግል እናያለን። ባዶ ቃላት አይደለም ማሪያም የተናገረችው። በተጨማሪም፣ ለዮሴፍ እንዲሁም በኋላም ለኢየሱስ ታዛዥ ነበረች። ለዚህ ከመጽሐፍ ቅዱሳችን ምን ምሳሌዎች ማሳየት እንችላለን?

- ማሪያም የኢየሱስ እናት ትሆኚለሽ ከተባለች በት ጊዜ ጀምሮ በእርግዝናዋም፣ በወሊዷም፣ በኢየሱስ እድገትና ሕይወት፣ እንዲሁም በሞቱ ውስጥ ሁሉ ብዙ ፈተና፣ ስቃይ፣ እና መከራ ደርሶባታል። ከእግዚአብሔር ቃል እስቲ ከእነዚህ አንድ አንዶቹን እንቃኝ።

- እግዚአብሔር ማርያምን ለመባረክ እንዴት/ለምን መረጣት? እግዚአብሔር እኛንስ ለመባረክ እንዴት/ለምን ይመርጣል?

Selah
PAUSE · REFLECT

# የአሰላስሎት ጥያቄዎች

ከማርያም ሕይወት አንድ ልንማር የምንችለው ነገር ምን ያህል ከእግዚአብሔር ቃል ራሷን ያቀራረበች ሰው መሆኗን ነው። እኛስ ምን ያህል ራሳችንን ከእግዚአብሔር ቃል ጋር አቀራርበን እየኖርን ነው? በቃሉ ውስጥ የምናሳልፈውን ጊዜ እንዴት መጨመር ወይም የበለጠ ምርታማ ማረግ እንችላለን?

እግዚአብሔርን መታዘዝ የሚመችም የማይመችም ውጤት ይዞ ሊመጣ ይችላል። እሱን ለመወጣት ግን ብርታት ይሰጠናል፤ እንዲሁም መስዋእትነት የሚከፍለውን ሰው ጌታ አይረሳም። አንዴ ኢየሱስን ከወለደች በኋላ እግዚአብሔር ማሪያምን አልተዋትም። መላው ቤተሰቧን ከመጠበቅ እንዲሁም የወደፊት ሕይወቷን አመቻችቷል። ይህ ለጌታ ደፋር ምርጫዎችን እንድናደርግ እንዴት እንደሚያበረታታን እናስብ። እስቲ ዛሬ የሚነግረንን እንስማ። ጥሪውን እንድንቀበል፣ እንደ ማሪያም እምነት እንዲሰጠን እንለምነው።

ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም። ድንግል እንድትፀነስ ማድረግ ከቻለ ዓላማዎቹን ለመፈፀም ከተፈጥሮ ሕጎች በላይ መሄድ ይችላል ማለት ነው። በሕይወታችን ውስጥ፣ ምንም ያህል ትልቅም ይሁን ከባድ እግዚአብሔር ማንኛውንም መሰናክሎች ሊያሸንፍ ይችላል። እግዚአብሔር በፊታችሁ ያለውን ትልቅ መሰናክል ስላሸነፈበት ጊዜ  እናስብ፤ ጌታ እንዴት ረዳን?

እኛ ራሳችንን ብንመረምር፣ እውነት የክርስቶስ ባሪያዎች ነን?

Selah
PAUSE · REFLECT

# ማስታወሻ



Selah
PAUSE • REFLECT

# ጥበብ

የእግዚአብሔር ሕግ ፍጹም ነው፤ ነፍስንም መልሶ ያለመልማል፤ የእግዚአብሔር ሥርዐት የታመነ ነው፤ አላዋቂውን ጥበበኛ ያደርጋል።

መዝሙር 19:7

**ሁሉንም የሴላ ጥበብ ጥናቶች ለማግኘት**

[www.selahethiopia.org/studies](www.selahethiopia.org/studies)